ስማችን ኢወክንድ
ልሳናችን ነቅንቅ

ጥቅምት 26 2003 ዓም

# ልዩ መግለጫ

ሠማዕታት ሲታሰቡ :-

የወንድም አህቶቻችንን ደም !!
እንፋረዳለን
እንበቀላለንም::

የእናት አባቶቻችንና የእኛም ድምፅ ይከበር ብለው በገዛ ሀገራቸው በሠላም ሠልፍ የወጡ አፍላ ጀግኖቻችን በአረመኔው የወያኔ ቡድን ከታረዱ እነሆ ዛሬ 5ኛ ዓመታቸው ሲሆን ይህን ቀን ኢወክንድ የሚያከብረው በሀ ዘንና በቁዘማ ሳይሆን በብሔራዊ እልህና ቆጭት ነው::

በኢትዮጵያ ወጣት ደም በመለቃለቅ ኢትዮጵያዊ የሚኮን የሚመስለው የታሪክ አተላ የሆነው የዘረኞች ጥርቅ ም ወያኔ ሃርነት ትግራይ የዛሬ አምስት ዓመት በየአደባባዩ የፈጃቸውወንድም እህቶቻችን፥ አብሮ-አደግ ጓደ ኞቻችን ደማቸው ደመ-ከልብ እንደማይሆን ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ፥ በቃልኪዳን ማኅተማችን ኢወክንድ በ ሚል መጠሪያ ከተደራጀን እነሆ አንድ ዓመት ከመንፈቅ ሆኖናል ::

የጓደኞቻችን የሢቃ ድምፅ ይሠማናል ፥

የጣዕር ዕሪታቸው ያቃጭልብናል ፥

በሀርነት ትግራይ ገዳዮች የፈሰሰው ደማቸው ይጠራናል ፥

እንፋሎቱ እነሆ አስከ ዛሬ ድረስ ይፈጀናል ፥

ለዚህም ነው :-

ወንድሙን ሲገድሉት ወንድሙ ካልከፋው ፥

አምጡለት ሱሪውን ደሙ እንዲከረፋው ::

ተብሎ የተቋጠረው ሥንኝ እንዳይቋጠርብን ስንል ነው !

ዛሬ በመግለጫችን የጓደኞቻችንን ደም በሥነ ሥርዓቱ እንደምንበቀል የምናረጋግጠው !

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: joineprpyl@gmail.com
www.eprpy.com

የዛሬ አምስት ዓመት ከተወሳማ !! ወደ ደዴሳ አግዘውን በእባብ አስነድፈውናል ፡፡ በጊንጥ አስወግተውናል ፡፡ በአዞ አስገምጠውናል፡፡ በዘንዶ አስውጠውናል፡፡ በሸዋሮቢት በብርሽለቆ፥ በዝዋይ ፥ በቃሊቲ እስርቤቶች በ ዘር ጥላቻ በታጨቀ የበቀል ስሜት ተቀጥቅጠናል፡፡

ለማስፈራሪያ ተብሎ ከደዴሳ የናዚው ወያኔ ማጎሪያ ከአጠገባችን ጓደኞቻችን የሆኑ እየተወሰዱ አንገታቸውን በካራ አርደው አምጥተው “ ሊያመልጡ ሲሉ አዞ በላው/ በላትእያሉ ፥እንካችሁ የተረፈው አንገት ቅበሩ እያሉን እንደ ቆሻሻ በላስቲክ ጠቅለለን ቀብረናል፡፡

ታዲያ ይህንን ድርጊት የፈፀመብን ማንም ሳይሆን፥ የባዕድ ሎሌዎች የሆኑ ፀረ ኢትዮጵያውያን ጥቂት የትግ ራይ መሳፍንትና አንጋችና አንጋቾች ብቻ ናቸው፡፡

ይህ በዜጎቻችን ደም የተነከረው የጨቀየ ዘረኛ ሥርዓት ከስሩ መመንገልና / መደምሰስ አለበት የምንለ ው ከተራ ቂም-በቀል ሳይሆን ሀገራችንን ይዟት እየጠፋ ካለው ቡድን ማዳን አለብን ከሚል ጽኑ አቋም ነ ው፡፡ የዛሬ አምስት አመት በዘረኞች የታረዱት የእህታችን ወጣት ሽብሬ፥ የእህታችን ወጣት መሠረት ታደ ሠ የነ ወጣት ነብየ ልዑል የህፃን ያሲንና እንዲሁም ባለፉት አስራ ዘጠኝ ዓመታት ከወያኔ ጋር ሲፋለሙ ሰማ ዕታት የሆኑትን እነ ገብረ እግዚአብሔው ወልደ ሚካኤል (ጋይም)፥ እነ ተስፋዬ ታደሰ፣ እነ አሰፋ ማሩ ወዘ ተ.. ወይም መዳረሻቸው የጠፋውን እነ ፀጋዬ ደብተራውንና ጓደኞቹን የምንዘክራቸው ለቀን ቆጠራ ወይም ለፍቅር መግለጫ ብቻ ሳይሆን ፥ እንደ ኢወክንድ ዕምነት አቅማችንን አጎልብተን ከሁሉም መስል አቋም ካላ ቸውና በኢትዮጵያዊ ድርጅት ስር ከተደራጁ እንዲሁም ካልተደራጁና ግን ቆራጥ ውሳኔ ካላቸው ወጣቶች ጋር የትግል አንድነት ፈጥረንና ተባብረን ወያኔን ለመፋለምና ቀብሩን ለማቅረብ ነው፡፡ በመሆኑን በዚህ አጋ ጣሚ የእንፋለምና የሀገር አድን ጥሪ እናስተላልፋለን ፡

የአሁኑም ይሁን የቀደሙ ሰማዕቲቻችን ምን ጊዜም ህያው ናቸው !

የወያኔ ሥርዓት ይ ገረሰሳል !

ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊ ነች !

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት

(ኢወክንድ)

EPRPYL